# የስታርታፕ እና ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ አሰጣጥ መመሪያ ማብራሪያ

## መግቢያ

የስታርታፕ ስራ ፈጠራ በባህሪው በፈጣን ለውጥና በከፍተኛ ስጋት ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ግልጽ በሆኑ የአሰራር መመሪያዎች መመራቱ ለዘላቂ ስኬቱ መሰረት ነው በኢትዮጵያም የስታርታፕ አዋጅ መውጣቱ ሃሳብ ያላቸውም ሆነ ድርጅቶች በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው መንቀሳቀስ እንዲችሉ ትልቅ ዕድል የፈጠረ ሲሆን መመሪያዎች መኖራቸው ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ግልጽነትን በመፍጠር በባለቤቶችና በሰራተኞች መካከል ሊነሱ የሚችሉ አለመግባባቶችን ቀድሞ ለመፍታትና የሀብት ብክነትን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ጠንካራ የህግ መሰረት መኖሩ የውጭ ባለሀብቶች በስታርታፖች ላይ እምነት አሳድረው ካፒታላቸውን እንዲያፈሱ የሚያበረታታ ሲሆን በተለይም የአእምሯዊ ንብረት መብትን በማስከበር ረገድ የፈጠራ ውጤቶች በሌሎች እንዳይሰረቁ ወይም እንዳይቀዱ ዋስትና ይሰጣል፡፡ በመሆኑም ስታርታፖች ከመንግስት የሚሰጡ የታክስ እረፍቶችንና የተለያዩ ማበረታቻዎችን ለማግኘት እንዲሁም ወደ ትልቅ ተቋም ለማደግ የሚያስችላቸውን የህግ ማዕቀፍ እንዲኖርና የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የውስጥ መመሪያዎችን ማውጣት እንደ አማራጭ ሳይሆን እንደ ዋነኛ የንግድ ስትራቴጂ ሊወሰድ ይገባል፡፡

መመሪያው በስታርታፕ አዋጅ ቁጥር 1396/2018 መሰረት የተዘጋጀ እና አዋጁን ወደ መሬት ለማውረድ የሚያስችል እና ዕለት በዕለት ለሚያጋጥሙ ኦፕሬሽናል ስራዎችን ለመምራት እንዲሁም ስታርታፖች እና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች በሃገራችን የአዳዲስ ፈጠራ ስራዎች እና ገበያ ላይ እንዲያብቡ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥር ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ መመሪያ ኢኖቬሽንን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ ቴክኖሎጂን ወይም በቴክኖሎጂ የታገዙ ምርቶች፣ አገልግሎቶች ወይም ሂደቶች በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ ዋጋ የሚፈጥሩ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ኩባንያዎች (ስታርታፖች) እንዲሁም የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች (እንደ ኢንኩቤተር፣ አክስለሬተር፣ የጋራ መስሪያ ቦታ፣ ቬንቸር ካፒታልና ኤንጅል ኢንቨስተሮች) ስያሜ ለማግኘት የሚያስችላቸውን ስርዓት በመዘርጋት ተዓማኒ የሆኑና በገበያ ውስጥ የማደግ እና የመስፋፋት ተስፋ ያላቸውን ስታርታፖች የድጋፍ፣ የማበረታቻና የገበያ

እድሎችን እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር መንግስትም በዘርፉ ሊኖረው የሚገባውን ሚናም በአግባቡ ለመጫወት ያስችለዋል፡፡

## የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

በመመሪያው ውይይት ላይ የስራን ክህሎት ሚኒስቴር፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን፣ ኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስመንት ሆልዲንግ፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

የመመሪያው ዝርዝር ይዘቶች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው እና ከላይ ከተጠቀሱት የመንግስት ተቋማት ጋር በተወካዮቻቸው አማካኝነት ተሳትፎ እንዲደርጉ በማድረግ በዝርዝር ውይይት የተካሄደበትና ከተሳታፊዎች የቀረቡ ገንቢ ሃሳቦችን በመውሰድ መመሪያውን የማጎልበት ስራ ተሰርቷል፡፡

እንዲሁም መመሪያው ፍትህ ሚኒስቴር ባለማው የአስተያየት ወይም ግብአት መሰብሰቢያ ላይ በመጫን ለአስተያየት ክፍት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የማዳበር ስራ ተሰርቷል፡፡

## የሃገራት ተሞክሮ

የስታርታፕ ማመልከቻ አቀራረብና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በብዙ ሃገሮች ተመሳሳይና ተቀራራቢ ሲሆን በተለይም ማመልከቻው ሲቀርብና ተከታታይ ሁኔታዎች በሙሉ በቴክኖሎጂ በታገዘና ኦንላይን እንዲሆን ግልጽነትና ተጠያቂነትን (Transparency and Accountability) ለማስፈን የኦንላይን ፕላትፎርም ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ የምዝገባ ሂደቱ በሰው ንክኪ እንዳይበላሽና ለሁሉም አመልካቾች እኩል ዕድል እንዲሰጥ ያደረጋሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ተሞክሮ ቱኒዝያ፣ ኢስቶኒያ እና ህንድ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በፈረንሳይ "La French Tech" የተባለው የመንግስት ተነሳሽነት ስታርታፖችን የመለየትና የማረጋገጥ ስልጣን ያለው ሲሆን በተለይም እንደ "French Tech Visa" ያሉ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን ለመስጠት ድርጅቱ በእርግጥም የፈጠራ ስራ (Innovative) መሆኑን የሚገመግም የባለሙያዎች ቡድን አለው፡፡ ይህ ቡድን እንደ ኢትዮጵያው ብሄራዊ ስያሜ

ኮሚቴ ሁሉ አንድ ድርጅት "ስታርታፕ" ተብሎ እንዲጠራና የመንግስት ድጋፍ እንዲያገኝ መስፈርቱን ማሟላቱን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡

በሲንጋፖር ደግሞ "Enterprise Singapore" የተባለው የመንግስት አካል በስሩ ባሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች ለምሳሌ እንደ "Startup SG" ባሉ ማዕቀፎች አማካኝነት ስታርታፖችን የመመዝገብና የመለየት ስራ ይሰራል፡፡ ሲንጋፖር የጥቅም ግጭትንና ግልጽነትን ለማረጋገጥ ኮሚቴዎቿን ከግል ዘርፉ ባለሙያዎችና ከመንግስት ስራ አስፈጻሚዎች የምታዋቅር ሲሆን የስታርታፕ ስነ-ምህዳር ውስጥ በአዋጁ የተቀመጠውን ብሔራዊ የስያሜ ኮሚቴ ተመሳሳይ ወጥ አካል ባይኖርም ተግባሩን የሚያከናውኑ ተመሳሳይ የባለሙያዎች ስብስብና ተቋማት መኖራቸውን ከግንዛቤ በመክተት በዚህ መመሪያ ገለልተኛና ሙያዊ ኮሚቴ የማቋቋም ዓላማ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## ዋና ዋና ክፍሎች

መመሪያው በሰባት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን፦

**ክፍል** 1 ጠቅላላ ድንጋጌዎች የመመሪያው መጠሪያ ስም የተገለጸበት አጭር ርዕስ፣ በመመሪያው የተካተቱ ሆነው በአዲስነታቸው ምክንያት ወይም ግልጽነት ይጎድላቸዋል ወይም አሻሚ ትርጓሜ ይኖራቸዋል ተብለው የታሰቡ ቃላቶችን ወጥ ትርጉም እንዲይዙ ለማድረግ የተሞከረበት የትርጉም አንቀጽ፣ እንዲሁም ሚስጥራዊነት፣ መርሆችና የመመሪያውን ወሰን የያዘ ነው፡፡

**በክፍል** 2 የተቀመጠው ስያሜ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ሂደት ሲሆን በውስጡ ለአመልካቾች ጥሪ ማድረግ፣ ኦንላይን ፕላትፎርም አጠቃቀም፣ የማመልከቻ ዝርዝር መስፈርቶችና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ በተመለከተ የተገለጸበት ክፍል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ስታርታፖች ፕሮፖዛል እና ፕረዘንቴሽን ማቅረብ አለባቸው፡፡

የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ በመመሪያው የተቀመጡት ዝርዝር የማመልከቻ ማቅረቢያ ሁኔታና መስፈርቶቹ የትክክለኛ ሃሳብ ባለቤት የሆኑ ስታርታፖችን የጥራት መቆጣጠሪያ መንገዶች ሲሆኑ የእውነተኛነት ማረጋገጫ (Vetting and Validation) ሲሆን ይህም በዓለማቀፍ ደረጃ ስታርታፖች የሚሰጣቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ለምሳሌ የታክስ እረፍትና የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ፕሮፖዛልና ፕረዘንቴሽን እንዲቀርብ የሚደረገው

ድርጅቱ በእርግጥም አዲስና የፈጠራ ስራ (Innovation) የያዘ መሆኑን እንዲሁም ሊያድግ የሚችል (Scalability) መሆኑን ባለሙያዎች እንዲመዝኑት ለማስቻልና ተራ የንግድ ድርጅቶች የስታርታፕ ስያሜን በመውሰድ መንግስታዊ ማበረታቻዎችን ያለአግባብ እንዳይጠቀሙ ለመከላከል፤

በተጨማሪም አሰራሩ ግልጽነትና ተጠያቂነትን (Transparency and Accountability) በማስፈን የኦንላይን ፕላትፎርም ጥቅም ላይ የሚውለው የምዝገባ ሂደቱ በሰው ንክኪ እንዳይበላሽና ለሁሉም አመልካቾች እኩል ዕድል እንዲሰጥ ነው ይህም እንደ ኢስቶኒያና ህንድ ባሉ በስታርታፕ በበለጸጉ ሀገራት የተለመደ አሰራር ሲሆን አመልካቾች በማንኛውም ሰዓት ያሉበትን ደረጃ እንዲያውቁና አድሎአዊ አሰራርን ለመቀነስ ታስቦ በመሆኑ፤

በመጨረሻም የኢንቨስትመንት ዝግጁነትን (Investor Readiness) ማሳደግ ነው ስታርታፖች ፕሮፖዛልና ፕረዘንቴሽን እንዲያዘጋጁ ሲገደዱ የራሳቸውን የንግድ ሞዴልና ገበያ ጠንቅቀው እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል። ይህም ለወደፊቱ ከዓለማቀፍ ባለሀብቶች ጋር ለሚያደርጉት የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት እንደ ትልቅ ልምምድ የሚያገለግል ሲሆን እነዚህ መስፈርቶች የስታርታፕ ስነ-ምህዳሩ (Ecosystem) ጥራት ባላቸውና ውጤታማ በሆኑ ዓቅም ባላቸው የኃሳብ ባለቤቶች ብቻ የተሞላ እንዲሆን በማድረግ የሀገርን የፈጠራ ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚረዱ ናቸው።

**በክፍል 3** የተቀመጠው ስለ ብሔራዊ የስያሜ ኮሚቴ አወቃቀርና አገልግሎት ሲሆን በውስጡ ብሄራዊ ስያሜ ኮሚቴ አባላት፣ የአገልግሎት ዘመን፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ጥቅም ግጭትና ከአባልነት መነሳትን የተመለከቱ ድንጋጎችን ይዟል። ኮሚቴው ማመልከቻዎችን በመገምገም ስያሜ እንደሚሰጥ የሚያመላክት አንቀጾች ተካተውበት ይገኛሉ።

የብሔራዊ የስያሜ ኮሚቴ አወቃቀርና አሰራር በመመሪያው በዝርዝር ሲቀመጥ የስታርታፕ ስነ-ምህዳሩ በገለልተኛነት፣ በሙያዊ ብቃትና በታማኝነት እንዲመራ ለማስቻል ነው ኮሚቴው የተለያዩ የዘርፍ ባለሙያዎችን በማካተት ማመልከቻዎች ከአንድ ወገን እይታ ወጥተው በቴክኖሎጂ፣ በንግድ አዋጭነትና በህጋዊ መስፈርቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲገመገሙ ይረዳል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አሰራሩ በአንድ ግለሰብ ፍላጎት ስር እንዳይወድቅና ተከታታይነት ያለው የለውጥ መንፈስ እንዲኖር ለማድረግ የአገልግሎት ዘመንና ከአባልነት መነሳትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል። በተለይም የጥቅም ግጭትን (Conflict of

Interest) የሚመለከቱ ህጎች መካተታቸው ማንኛውም የኮሚቴ አባል ከሚያውቀው ወይም ከሚቀርበው አመልካች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካለው ራሱን ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዲያገል በማድረግ የሙስና ስጋትን ለመቀነስና በውሳኔዎች ላይ የህዝብና የባለሀብቶችን እምነት ለመገንባት ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህንንን መሰል አሰራር እንደ ፈረንሳይና ሲንጋፖር ባሉ ሀገራት የሚሰራበት የላቀ ተሞክሮ ሲሆን የስታርታፕ ስያሜ አሰጣጥ ሂደቱ በግልጽ የህግ ማዕቀፍ ተለይቶ መቀመጡ ተቋማዊ ተጠያቂነትን ከማስፈኑም በላይ የሀገሪቱን የስታርታፕ ፈጠራ ስራ ድጋፍ ስርዓት ፍትሃዊና ዓለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ያደርገዋል፡፡ ሌላው ደግሞ የስነምግባር ጉድለት፣ ከተወከለበት ተቋም መልቀቅ፣ የጤና እክል ወይም ሞት በመኖሩ የኮሚቴ አባል ከአባልነት ሊነሳ እንደሚችል በመግለጽ የኮሚቴው ብቃትና ቀጣይነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

**በክፍል** 4 የተቀመጠው ደግሞ የስታርታፕ ተዋንያን ተግባርና ሃላፊነት ሲሆን በውስጡ የሚኒስቴሩ፣ የስያሜ ኮሚቴ፣ ስታርታፖችና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች ተግባራት ተመላክቷል፡፡ ሚኒስቴሩ በአዋጁና በመመሪያው የተሰጡትን ኃላፊነቶች በሙሉ እንዲፈጽም ያስገድዳል፡፡ እንዲሁም የብሄራዊ የስያሜ ኮሚቴው ሥራ በተገቢ ሁኔታ እንዲከናወን የአገልግሎት ክፍያ፣ የመስሪያ ቦታ፣ የስራ መሳሪያ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን መሟላት እንደሚገባው ያብራራል፡፡ ይህ ድንጋጌ የኮሚቴውን ነጻነት በመጠበቅ ውጤታማ አፈጻጸም እንዲኖር ያግዛል፡፡

ሌላው በዚህ ክፍል የተቀመጠው ደግሞ የስያሜ ሂደት በግልጽ፣ በቴክኒክ እና በባለሙያዊ እይታ እንዲከናወን የኮሚቴውን ሚና ያብራራል፡፡ ማመልከቻዎችን በፕላትፎርም መመርመር፣ በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት ግምገማ ማድረግ እና የግምገማ ውጤቶችን ከዝርዝር መረጃ ጋር ለሚኒስቴሩ መላክ የውሳኔ ታማኝነትና ተጠያቂነት እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ባለሙያዎችን በpanel review ማሳተፍ የግምገማውን ጥራት ያሻሽላል፡፡

ሌላው የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ተገልጿል፡፡ ለኮሚቴ አባላት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ሙያዊ ግምገማ ላይ እንዲበረታ የሚያግዝ መሆኑን ያብራራል፡፡ ክፍያው የሙያ አበል መሆኑ የኢኮኖሚ ሁኔታን እና የስራ ጫናን እንዲያስተካክል ይረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስታርታፑ በእድገት ደረጃው መሰረት የሚጠበቅበትን የአፈጻጸም መጠን ያብራራል፡፡ የስያሜና የድጋፍ ቀጣይነት በተመጣጣኝ ውጤት ላይ እንዲመሰረት ያደርጋል፤ እንዲሁም ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ መገደዱ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን ያጠናክራል፡፡ ሌላው እና

የመጨረሻው የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች የሚሰጡት ድጋፎች ከአድሎአዊነት ነጻ፣ ግልጸኝነትን የተላበሰ እና በመደበኛ ስታንዳርድ እንዲፈጸሙ ያብራራል፡፡ በውጤት ላይ የተመሰረተ ግምገማና ክትትል ማድረግ እና ወቅታዊ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለባቸው በመግለጽ የስታርታፕ ምህዳሩ ጥራትና ዘላቂነት እንዲጠናከር ያግዛል፡፡

**በክፍል 5** የተመላከተው ደግሞ ስያሜ ላገኙ ስታርታፕ ሊኖራቸው የሚገባ ደረጃና መስፈርቶች የሚገልጹ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው፡፡ የስታርታፕ ስያሜ ሶስት ደረጃዎች ማለትም የመጀመሪያ፣ ድህረ መጀመሪያ እና ተመንዳጊነትና ሽግግር ደረጃን የሚያብራራ ሲሆን የስታርታፕ ምህዳር በደረጃ የተዋቀረና ስታርታፖች በቆይታቸው የሚገኙበትን የእድገት ደረጃ በግልጽ በመለየት፣ የሚደረግላቸውን እገዛ ወይም ድጋፍ ከእድገታቸው ጋር ተመጣጣኝ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የስታርታፕ የእድገት ጉዞን፣ በዕድሜ፣ በአፈጻጸም እና በገበያ ተፅዕኖ መሰረት ለመከታተል እና ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ያለው አስተዋጻኦ እጅግ የጎላ በመሆኑ ነው፡፡

የብቃት መስፈርቶች መዘርዘራቸው ስታርታፖች በእያንዳንዱ የእድገት ደረጃ ላይ ከእነርሱ የሚጠበቀውን የቴክኒክ፣ የገበያ፣ የፋይናንስ እና የድርጅታዊ አቅም እንዲያሳዩ ለማድረግ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በሃሳብ ጥራትና የችግር መፍትሄ ላይ፣ በድህረ መጀመሪያ ደረጃ በPMF፣ ገቢ እና የቢዝነስ ሞዴል ላይ በተመንዳጊነትና ሽግግር ደረጃ ደግሞ በፍጥነት እድገት፣ (exponential growth) በገበያ ድርሻ እና በመውጫ (exit) ዝግጁነት ላይ ትኩረት መደረጉ የደረጃዎች ተፈጥሯዊ ልዩነትን ያንጸባርቃል፡፡

**የመጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ**

የመጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ ለመባል አዲስ የመነጨና ወደ እቅድ የተቀየረ የስታርታፕ ጽንሰሃሳብ፣ ፈጠራ እና የተደራጀ መስራች መኖሩን ማረጋገጫ በማቅረብ እንዲሁም የስታርታፕ ጽንሰ ሃሳብን በተግባር መሞከር የሚያስችል መሰረታዊ የተግባር መስፈርት የሚያሟላ ምርት/ ፕሮቶታይፕ ( Minimum Viable Product) ተግባራዊ ማድረግ፣ ምርቱ የታቀደውን መስፈርት ማሟላቱን ማረጋገጥ እና የምርት አፈጻጸም ደረጃና ብቃት የሚያመላክት ዳታ መሰብሰብና ማሻሻያ መተግበሩን የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ፣ የስታርታፕ መስራቾች መሰረታዊ የተግባር መስፈርት የሚያሟላ ምርት ለመተግበር ከውጭ ፈንድ ወይም

ሌላ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው በሆነ ጊዜ ከኢንቨስተሮች ወይም ከመንግስት ፕሪ ሲድ ወይም ግራንት ማግኘት መቻላቸውን ማሳየት ለስታርታፕ ዕድገቱ አዋጪ መንገድ መሆኑ ቢታወቅም ስታርታፕ መስራቹ ከውጪ ግራንት ወይም ፕሪሲድ ፈንድ ወይም ድጋፍ ሳያስፈልገው በውስጥ አቅሙ ተመሳሳይ መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ ምርት ማቅረብ መቻላቸውን ማሳየት፣ መሰረታዊ የተግባር መስፈርት ያሟላው ምርት ከገበያ ፍላጎት ጋር ያለውን መጣጣም በተግባር መፈተሽና የገበያ ዳታ/ መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል ለገበያ ፍላጎት ተስማሚ ምርት (Product Market Fit) የመጀመሪያ ገበያ ሙከራ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህም ምርቱን ከመስራቾቹ ውጭ የሚመነጭ ድጋፍ እና ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ሲድ ፈንድ ወይም ግራንት የሚያሳይ መረጃ ለስታርታፕ ዕድገቱ አዋጪ መንገድ መሆኑ ቢታወቅም ስታርታፕ መስራቹ ከውጨ ግራንት ወይም ሲድ ፈንድ ወይም ድጋፍ ሳያስፈልገው በውስጥ አቅሙ የመጀመሪያ ደረጃ ምዕራፍ ፍላጎት ተስማሚ ምርት (Product Market Fit) የመጀመሪያ ገበያ ሙከራ መረጃ ማቅረብ እና በዚህ ደረጃ የሚገኝ ስታርታፕ አጠቃላይ በስታርታፑ የጽንሰሃሳብ ዝግጅት መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ ምርት ወይም ለገበያ ፍላጎት ተስማሚ ምርት በሚከወንበት ሂደት ከውጭ ወይም ከውስጥ በስታርታፕ ሃሳቡ ላይ የዋለ ፈንድ ድጋፍ የኢንኩቤሽንና አክስለሬሽን ተሳትፎ እንድሁም የስታርታፕ አሁናዊና መጻኢ የገበያ ግምት እና ከሙከራ ወደ ተዋቀረ እድገት ሽግግር መረጃ በገበያ ግብረመልስ ገቢ ለማመንጨት አዲስ መንገድ ሲፈለግ ወይም በሌላ ውጫዊና ቴክኒካዊ ለውጦች ተነስተው አቅጣጫ ሲቀይሩ በመማር ላይ የተመሰረተ የስትራቴጂ አቅጣጫ ለውጥ (Pivot) የሚያሳይ ማስረጃና ሪፖርት የሚያሳይ በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት አንቀጾች በተቀመጡ ተግባራት ውስጥ የኢኖቬሽን፣ የተመንጻጊነት፣ የቴክኖሎጂ ወይም በቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን እና የገበያ መዋቅር መቀየሩን እምቅ አቅም ማሳያዎች በኢንደስትሪው መለኪያ መስፈርቶችና ቀመሮች እና የትግበራ መረጃ ወይም ዳታ መሰረት በማድረግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ድህረ መጀመሪያ ደረጃ

ስታርታፑ ድህረ መጀመሪያ ደረጃ ለማግኘት ከገበያ ፍላጎት ጋር ያለውን መጣጣም በተግባር መፈተሽና የገበያ ዳታ/ መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል ለገበያ ፍላጎት ተስማሚ ምርት (Product Market Fit)፣ የተደራጀ ገቢ እና የደንበኛ መጠን እንዲሁም የተደራጀ የቢዝነስ ሞዴል

መረጋገጥ ተከታታይ ማረጋገጫ ተግባራዊ የተደረገበትን ማረጋገጫ እና በዚህም ምርቱን ከመስራቾቹ ውጭ የሚመነጭ ድጋፍ እና ኢንስቨትመንት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ የግራንት ወይም ሲድ ወይም የመጀመሪያ ዙር ፈንድ እና ገቢ ፍሰት የሚያሳይ መረጃ እንዲሁም ለስታርታፕ ዕድገቱ አዋጪ መንገድ መሆኑ ቢታወቅም ስታርታፕ መስራቹ ከውጪ የግራንት ወይም ሲድ ፈንድ ወይም የመጀመሪያ ዙር የዕድገት ፈንድ ወይም ድጋፍ ሳያስፈልገው በውስጥ ገቢው ቀጣይነት ያለው የገበያ እድገት ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

በዚህ ደረጃ የሚገኝ ስታርታፕ አጠቃላይ በስታርታፑ እድገት ላይ የዋለ ፈንድ ኢንቨስትር እና ሌሎች ምህዳር ገንቢ ጋር ያሉ ስትራቴጂካዊ የቢዝነስ አጋርነት ድጋፍ እንዲሁም የስታርታፕ አሁናዊና መጻኢ የገበያና ኢንቨስትመንት አዝማሚያ አመላካች እና የእድገት ስትራቴጂ (Market Penetration / Development) መረጃ ማቅረብ እና በተገለጹት ተግባራት ውስጥ የኢኖቬሽን፣ የተመንዳጊነት፣ የቴክኖሎጂ ወይም በቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን እና የገበያ መዋቅር መቀየሩን እምቅ አቅም ማሳያዎች በኢንደስትሪው መለኪያ መስፈርቶችና ቀመሮች እና የትግበራ መረጃ ወይም ዳታ መሰረት በማድረግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### ተመንዳጊ እና ሽግግር የእድገት ደረጃ

ሶስተኛውና የመጨረሻ የስታርታፕ ስያሜ ደረጃ ተመንዳጊ እና ሽግግር የእድገት ደረጃ ሲሆን ይህንን ደረጃ ስያሜ ለማግኘት የስታርታፑ ገቢ በተረጋጋ እና በፍጥነት እያደገ መሆኑን፣ የቢዝነስ ሂደት ተገማችና አስተማማኝነት፣ የሰው ሃይል ተሳትፎ እድገት መኖር፣ ሚዛናዊ ወጪና ገቢ እየጨመረ መሄዱን የሚያመላክት እና በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ ወይም በአለም አቀፍ የገበያ መስፋፋትና ድርሻ መጠን የሚገለጽ ተመንዳጊነት (scaleup) ደረጃ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

እንዲሁም የውህደትና ግዥ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ የሕዝብ አክሲዮን አቅርቦት (IPO) እና የኢንቨስትመንት የመዋቅር ለውጥ ሽግግር ፍጻሜ መዳረሻ ወይም መውጫ ስትራቴጂና ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሌላው በዚህ ክፍል የተቀመጠው የስያሜ ዕድሳት ስርዓት መቀመጡ ስታርታፑ ስያሜውን ከተቀበለ በኋላ ተገቢ እድገት እያሳየ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ሂደት የአፈጻጸም ሪፖርትን በመጠየቅ እና ወደ ቀጣይ ደረጃ ለመሸጋገር ያለውን ብቃት በመመዘን የስያሜ

አጠቃቀም ተገቢነትን ያረጋግጣል፡፡ ሌላው የስያሜ እገዳ መቀመጡ የስታርታፕ ስያሜ ተጠቃሚነት እና አላማው እንዳይጣስ ለመከላከል ነው፡፡ ስያሜው ከተፈቀደለት አላማ ውጪ ሲውል፣ የመስራች ድርሻ ሲቀንስ ወይም የስታርታፕነት መገለጫ ሲጠፋ እገዳ መጣል የስርዓቱን ታማኝነት ይጠብቃል፡፡

የስያሜ መሻር የተደነገገው ስታርታፑ በሕግ እና በመመሪያው የተቀመጡ መስፈርቶችን በግልጽ ሁኔታ ሲጥስ ወይም የተሰጠውን የማሻሻያ ጊዜ ሳይጠቀም ሲቀር ተፈጻሚ እንዲሆን ነው፡፡ ይህ ደንጋጌ የስታርታፕ ስያሜ ክብርን እና ታማኝነትን ለመጠበቅ ዋና ሚና ይጫወታል፡ ፡

የመጨረሻው ደግሞ የውጭ ሃገር ስታርታፖችን በዚህ ስርዓት ውስጥ መካተታቸው የአገር ውስጥ የስታርታፕ ምህዳርን ለዓለምአቀፍ ተሳትፎ ክፍት ለማድረግ እና የቴክኖሎጂና የካፒታል ፍሰትን ለማበረታታት ነው፡፡ በኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ መመራታቸው የሀገር ውስጥ ፖሊሲዎች እንዲከበሩ ያደርጋል፡፡

**በክፍል** 6 የተገለጸው ደግሞ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች ስያሜ መደቦች ማለትም ኢንኩቤተር፣ አክስለሬተር ወዘተ የብቃት መስፈርቶች፣ ዕድሳት፣ እገዳና መሻር በተመለከተ የተቀመጠ ነው፡፡

መመሪያው የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎችን በኢንኩቤተር፣ አክስለሬተር፣ የጋራ መስሪያ ቦታ፣ ቬንቸር ካፒታል እና ኤንጅል ኢንቨስተር መደቦች በመከፋፈል ያቀርባል። የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች የሚያገኙትን ስያሜ ማደስ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የህም በየ5 ዓመት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ይህ ክፍፍል በስታርታፕ ዕድገት ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና፣ የሚሰጡትን ድጋፍ እና የአገልግሎት ደረጃ በግልጽ ለመለየት ያግዛል። እንዲሁም በስታርታፕ ምህዳር ውስጥ አዳዲስ የአገልግሎት አይነቶች ሲፈጠሩ ተጨማሪ መደቦች እንዲካተቱና በየጊዜው ለሚመጡ አዳዲስ አገልግሎቶችን እያካተቱ ለመሄድ ዕድል ይሰጣል፡፡

የብቁነት መስፈርቶቹ እያንዳንዱ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ መደብ በተግባር በስታርታፕ ዕድገት ላይ እውነተኛ እና ቀጣይነት ያለው ድጋፍ መስጠት እንዲችል ለማረጋገጥ ተዘጋጅተዋል። መስፈርቶቹ የፕሮግራም ይዘት፣ የሰው ኃይል ብቃት፣ የቆይታ ጊዜ፣ የመሠረተ

ልማት አቅም፣ የኢንቨስትመንት ግልጽነት እና የፈንድ ትስስርን በማካተት የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች በስም ብቻ ሳይሆን በተግባር ውጤታማ እንዲሆኑ ያስገድዳሉ። ለምሳሌ፡-

- **አክስለሬተር**

በዚህ መደብ ውስጥ ለመገኘት ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል ድህረ መጀመሪያ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ያሉ ስታርታፖችን የሚደግፍ ሆኖ የዕድገትና ተመንዳኒነት ስልቶች፣ ለኢንቨስትመንት ዝግጁነት፣ ጥልቀት ያለው የቢዝነስ ሞዴል ወደ ገበያ የመግባት ስልት ፣ የአመራርና የተቋማዊ መዋቅር ማሳደግ፣ የህግና ቁጥጥር ማሟላት እና የትስስር መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሌሎች የስታርታፕ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ያለው ወይም በሌላ የስታርታፕ ዕድገት ደረጃ ላይ አቅም ግንባታ ፕሮግራም የሚሰራ አቅም እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ የሚያቀርብ መሆን አንዱ ሲሆን ሌላው በተቋማዊ አደረጃጀት የተደራጁ እና በስታርታፕ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ልምድ ያላቸው ቢያንስ 3 ባለሙያዎች ኖሮት ፕሮግራሙን መምራት የሚያስችል የሰው ሃይል መኖር ይኖርበታል።

- **ቬንቸር ካፒታል**

በመመሪያው ቬንቸር ካፒታል ለመባል ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል እንደ ምሳሌ ለመመልከት ስታርታፕ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ የፈንድ ገንዘብ ያለው እና በስታርታፕ ላይ ካፒታሉን ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት ያለው መሆን፣ ከዚህ ቀደም በስታርታፕ የተሳኩ ኢንቨስትመንቶች መኖራቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያለው፣ በቴክኖሎጂው ዘርፍ ከፍተኛ የሥራ አመራር ልምድ ካለው እንዲሁም በድህረ መጀመሪያ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ባለ ስታርታፕ ላይ በማተኮር ካፒታሉን ኢንቨስት የሚያደርግ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን እንዳለበት ተቀምጧል።

- **ኤንጅል ኢንቨስተር**

በዚህ መደብ ውስጥ ለመገኘት በመጀመሪያ ደረጃ፣ በድህረ መጀመሪያ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ባለ ስታርታፕ ላይ ካፒታሉን ኢንቨስት የሚያደርግ፣ ስጋትን መቀነስ የሚያስችል ስትራቴጂ እንዳለው የሚያሳይ ሰነድ ያለው መሆኑን የሚያሳይ፣ ስታርታፑ ከተመንዳኒነት እና ሽግግር ደረጃ በኋላ ከሚገኘው ውጤት ወይም ስኬት ወይም ድርሻ ላይ ለመመለስ ወይም ለማግኘት መወሰኑን ማሳየት እንዲሁም በስታርታፑ ላይ ኢንቨስት ያደረገውን የገንዘብ መጠን፣

የወሰደውን የትርፍ ድርሻ እና የተዘጋጀ የመግባቢያ ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሌላው በመመሪያው የተቀመጠው ውስጥ የስያሜ ዕድሳት በተመለከተ መደንገጉ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች በቀጣይነት መመሪያውን እየጠበቁ መስራታቸውን ለመረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ የግልጽነትና የተጠያቂነት መንገድ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሚኒስቴሩም በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲሰጥ ያግዛል፡፡ በተጨማሪም የስያሜ እገዳ እና መሻር በተመለከተ የተደነገጉት ስያሜውን በተሳሳተ መንገድ እንዳይጠቀም ለመከላከል ነው፡፡ ይህ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች ተግባራቸውን ከተፈቀደው ዓላማ ውጪ እንዳይመሩ የሚያስጠነቅቅ መንገድ ሲሆን የምህዳሩን ጥራት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡

በመጨረሻም የተቀመጠው የውጭ ሀገር ስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች በአገር ውስጥ የሚሰሩ አካላት ጋር ተመጣጣኝ መመሪያ እንዲተገበርባቸው በመደንገግ፣ ፍትሃዊ ውድድርና የኢኮሲስተም ጥራት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የኢንቨስትመንት ህጎችን ከመከተል ጋር ዓለም አቀፍ ልምድና ካፒታል ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ያበረታታል፡፡

በአጠቃላይ በክፍሉ የተቀመጡት አንቀጾች የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች በተደራጀ፣ ተጠያቂነትን በተላበሰ እና ውጤታማ መንገድ እንዲሰሩ የሚያስችል መዋቅር ይፈጥራሉ፤ ይህም በሀገር ውስጥ የስታርታፕ ኢኮሲስተሙ እድገትና ተመንዳኒነት ላይ አስፈላጊ ሚና ይጫወታል፡፡

**በክፍል 7** የተቀመጠው ቅሬታ አፈታት የተመለከተ ሲሆን በውስጡ ኮሚቴ አባላት፣ ሂደትና ውሳኔ አሰጣጥን የሚያሳዩ አንቀጾች ተካተዋል፡፡ ቴክኒክ ቅሬታዎች ለስያሜ ኮሚቴ፣ አስተዳደራዊ ለቅሬታ ኮሚቴ ይላካሉ፡፡ ቅሬታው ለሚኒስትሩ የሚቀርብበት አግባብ በኮሚቴው የተወሰነው ውሳኔ ላይ በሚኒስትሩ መፈታ የሚችልበት አግባብ ካለ ክፍት የሚያደርግበት ሂደት ያለ ሲሆን ቅሬታው እስከ መደበኛ ፍርድቤት ድረስ እንደሚቀርብ ያሳያል፡፡

በዚህ ክፍል የቅሬታ ኮሚቴው ለሚኒስትሩ ተጠሪ መሆኑን በመደንገግ የአስተዳደራዊ ተጠያቂነትና የፖሊሲ አቅጣጫ ግልጽነትን ያረጋግጣል፡፡ ከተለያዩ ሚኒስቴሮችና የሙያ ማህበራት ተወካዮች የተዋቀረ መሆኑ ቅሬታዎች በብዙ ዘርፎች እይታ እንዲገመገሙ እና አንድ ተቋም ብቻ በሚያመጣው የውሳኔ አደጋ እንዳይገደቡ ያግዛል፡፡

ሌላው የቅሬታ አፈታት ሂደትን በቴክኒክ እና በአስተዳደራዊ ጉዳዮች በመለየት ያቀርባል። ቴክኒክ ቅሬታዎች በፍጥነት ወደ ስያሜ ኮሚቴ መላካቸው የሂደት መዘግየትን ለመከላከል ይረዳል፤ አስተዳደራዊ ቅሬታዎች ደግሞ በቅሬታ ኮሚቴው በጥልቀት እንዲመረመሩ ያስችላል። ለሂደቱ የስራ ቀናት ተወስነው መቀመጣቸው የተጠያቂነትን እና የአገልግሎት ፍጥነትን ያጠናክራል። የቅሬታ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ አቤቱታ ለሚኒስትሩ የማቅረብ መብት መኖሩ ተጨማሪ የፍትህ መጠየቂያ ሂደት ሆኖ ያገለግላል። በሚኒስትሩ ውሳኔው ቅር የተሰኘ አካል ይግባኝ ለመደበኛ ፍርድቤት እንደሚያቀርብ ተቀምጧል። ይህም ለቅሬታ አቅራቢዎች መብታቸው እንዳይገደብ ያደርገዋል።

ሌላው የኮሚቴው የአገልግሎት ጊዜ ሁለት ዓመት መሆኑ ተቋማዊ ቀጣይነትን እና የሥራ ልምድ መጠናከርን ያረጋግጣል። ለተጨማሪ አንድ ዙር የመመረጥ አማራጭ መኖሩ ደግሞ ውጤታማ አባላት ልምዳቸውን እንዲቀጥሉ ያበረታታል። የጥቅም ግጭትን በቅድሚያ መግለጽና ከውሳኔ ሂደት መራቅን በተመለከተ መቀመጡ የኮሚቴው ገለልተኛነትና ታማኝነት እንዲጠበቅ ያደርጋል። ይህ የቅሬታ አፈታት ሂደት በማንኛውም ዓይነት የግል ወይም የፋይናንስ ተፅዕኖ እንዳይበከል የሚያስጠነቅቅ ወይም የሚጠብቅ መንገድ ነው።

በአጠቃላይ የመመሪያው ክፍል ሰባት የቅሬታ አፈታትን በግልጽ፣ ፍትሃዊ እና በተጠያቂነት መንገድ ለማስፈጸም የሚያስችል የተደራጀ መዋቅር ይፈጥራል። ይህም በመመሪያው የሚሰጡ ውሳኔዎች ታማኝነትና ተቀባይነት እንዲኖራቸው አስፈላጊ ሚና ይጫወታል።

በመመሪያው ክፍል 8 ላይ ልዩ ድንጋጌዎችና ተፈጻሚነት በተመለከተ የተቀመጠ ሲሆን ሁሉም መረጃዎች በዳታ ጥበቃ ህግ መሰረት እንደሚጠበቁ፣ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽለው እንደሚችል፣ የመተባበር ግዴታ፣ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች እና ረቂቅ መመሪያው በሚኒስትሩ ተፈርሞ በፍትህ ሚኒስቴር ቁጥር ከተሰጠበት ጀምሮ ተግባር ላይ እንደሚውል አስቀምጧል። አጠቃላይ ይህ መመሪያ የስታርታፕ ምህዳርን ለማጠናከር፣ ኢኖቬሽንን ለማበረታታትና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማሳደግ ትልቅ ሚና ይጫወታል።